# መቃብር ቆፋሪ

የሚያደናግረው ፣ ግር የሚለው ለሰው
ጥርስ ያለው ወያኔ ፣ እየነካከሰው
አስዶ እየፈጀው ፣ እያተራመሰው
የዛሬው በደሉ ፣ የማይኮሰኩሰው
ወደፊት አይጓዝ ፣ ሁሌ የሚያነክሰው
መቶ ዓመት ፣ ኋልዮሽ የሚያመላልሰው
በየመቃብሩ ፣ የሚልከሰከሰው
ሚኒሊክ ተፈሪ ፣ እያለ የሚከሰው
በተቃጠለ ፊልም ፣ ዛሬም እሳት ጎርሰው
መች ይሆን ፅንፈኞች ፣ የሚያስቡ እንደሰው ።

የወንድም እህቱ ፣ የናትና አባቱ
ገዳዩ እያለለት ፣ ቆሞለት ከፊቱ
ዛሬ ላይ በሆነው ፣ የማይፀፀቱ
አፈር ለበላቸው ፣ አያት ቅድመአያቱ
ጥንት ያልነበሩትን ፣ ዛሬ መሞገቱ
ወደኋላ ሄዶ ፣ ገመድ መጓተቱ
በመቶ ዓመት ተረት ፣ በውዳሴ ከንቱ
ነገርን ማላዘን ፣ ላያደርገው ብርቱ
ባልኖረበት ዘመን ፣ ምን ያርገው ወጣቱ ።

እንኳን ሚኒሊክን ፣ ደርግን ለማያውቀው
ተረት ይሁን እውን ፣ ምንም ለማይደንቀው
ሃሜት አሉባልታ ፣ ላይበርደው ላይሞቀው
በነፃነት ትግል ፣ ጭምብል ያጠለቀው
የወጣቱን ስሜት ፣ ሃቁን እያወቀው
እንቅፋት ባይሆነው ፣ ቢጓዝ ወደላቀው
ታሪክ ባያጎድፉ ፣ እውነትን ደብቀው ።

ከራሱም ተጣልቶ ፣ ካምላክ ከፈጣሪ
ሲያሻው ከሚኒሊክ ፣ ሲያሻው ከተፈሪ
እያነፈነፈ ፣ የሚኖር ጠብ ጫሪ
የዘር የጥላቻ ፣ ከዳሚ አጋፋሪ
አምናን ከዘንድሮ ፣ አይለይ አስቸጋሪ
ወደፊት አይጓዝ ፣ ቀኝ ኋላ ዘዋሪ
የዘመኑ ልሂቅ ፣ መቃብር ቆፋሪ
ሙታንን ይከሳል ፣ ከንቱ ቀባጣሪ
አልማዙ ያለቀ ክር ፣ አሰልቺ አሳፋሪ ።

ታዛቢው

September 19, 2018